# ዜና ዕረፍታ ለማርያም

## የእናታችን የድንግል ማርያም በዓለ  ዕረፍት ጥር 21 ቀን

መግቢያ

የተወደዳችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ምዕመናን እንኳን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ዕረፍት እግዚአብሔር በሰላም አደረሳችሁ በማለት ምስጋናዋ በደካሞች ፍጡራን አንደበት ሊነገር ይቅርና በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የሰባቱን ዕለታት ምስጋናዋን የደረሰው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ “እስመ ላእላዕ ወልቱት አነ” እኔ እርሷን ለማመስገን አንደበቴ ዱዳ፤ኮልታፋ ነኝ የድንግልን ውዳሴ እናገር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ላክልኝ እያለ ወደፈጣሪው ይለምን እንደነበረ በድርሰቱ ላይ በሰፊው ተገልጿል፡እኛም ከበረከቷ ለመሳተፍ ያህል እንጂ የእርሷን ምስጋና ለመግለጽም ሆነ ለመጻፍ ብቁ አይደለንም፡ለማለት ነው።

የሰማይና የምድር ንጉሥ እግዚአብሔር ቀዳማዊ አዳምን የፈጠረው ሺህ ዘመን ኖሮ፤ ዕፀ ሕይወትን በልቶ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነበር፡ ይሁን እንጂ መክፈልት ሲሹ መቅሰፍት እንዲሉ ምድራዊ ሥልጣን ሽቶ፡ ሕግን በመተላለፉ ሞትን አመጣ፡ “እግዚአብሔርሰ ኢገብረ ሞተ አላ ረሲዓን ሰብዕ ጸውዕዎ በቃሎሙ ወአርከ አምሰልዎ” እግዚአብሔርስ ሞትን አላደረገም በደለኞች  በቃላቸው ጠሩት እንጂ ወገንም አደረጉት ተብሎ እንደተጻፈ፡ ቀዳማዊ አዳም የሞት ተገዢ ሆነ  ፍትረቱ ሁሉ የአዳም ዘር ነውና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም  ምንም እንኳ ፈጣሪዋን የወለደች የአምላክ እናት ብትሆንም የሞት ጽዋን መቅመስ አልቀረላትም ለምንት ይዜኃር ኃያል በኃይሉ ወባዕል በብዝኃ ብዕሉ........ኃይለኛ በኃይሉ ለምን ይታበያል? ባለፀጋም በባለፀጋነቱ፤ ክርስቶስ ለእናቱ እንኳ ከሞት እንድትቀር አድልዎ አላደረገም፡ ሞትስ ሥጋ ለለበሰ ሁሉ ይገባል የማርያም ሞት ግን በሁሉ ዘንድ ያስደንቃል፡፡ ተብሎ እንደተጻፈ  የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በዓለ ዕረፍት መታሰቢያ በየዓመቱ በጥር 21 ቀን ለተከታዮቿ ምዕመናን የደወል ድምጽ አሰምታ በከበሮ በእንቢልታ፤ በታላቅ ውዳሴና ዝማሬ ታከብራለች፡፤ ለሰው ልጅ ሶስት አበይት መታሰቢያዎች አሉት፡፡1.ዜና ልደቱ፤ 2.ዜና ሕይወቱ 3.ዜና ሞቱ ናቸው።

### 1 ዜና ልደታ ለማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ እየተባለ የሚጠራው የብሉይ ዘመን ማክተሚያ ላይ በ5485 ዓመተ ዓለም ከአባቷ ከኢያቄም ከእናቷ ከቅድስት ሀና እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር  ግንቦት ሃያ አንድ ቀን በሊባኖስ ተራራ ተወለደች“ንዒ እምሊባኖስ እኅትየ መርዓት” እኅቴ ሙሽራዬ ከሊባኖስ ነይ (መኃ.4፤8) እያለ የነቢየ እግዚአብሔር የዳዊት ልጅ ብላቴናው ንጉሡ ሰሎሞን በቃለ አክብሮ፤ በቃለ አራኅርሆ የተቀኘላት በሊባኖስ እንደምትወለድ የእግዚአብሔር መንፈስ ገልጾለት ነበር፡፡

### 2 ዜና ሕይወታ ለማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቀድሞውንም የስዕለት ልጅ ናት በተወለደች በሶስት ዓመቷ የጡት መጥባት ወራት ሲያከትም ወላጆቿ  ኢያቄምና ሀና ወደቤተ መቅደስ ይዘዋት ሄዱ፡እበውዕ ቤተከ ምስለ መባዕየ ወእሁብ ብጽዓትየ ዘነበብኩ በአፉየ ዘዕቤ በከናፍርየ አመ ምንዳቤየ በመከራዬ ጊዜ በአፌ የተናገርኩትን፤ከንፈሮቼም ያሉትን ስዕለቴን ላንተ እፈጽማለሁ (መዝ 65፤14) ተብሎ የተጻፈውን አብነት በማድረግ ነው።ካህናቱ ተሰብስበው የምግቧን ነገር ሲማከሩ መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤል ኅብስት ሰማያዊ፤ጽዋ ሰማያዊ ይዞ ከሰማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ብሎ ርቦ ታየ፡ነቢይ ወሰማዕት ይለዋል ካህኑ ዘካርያስ ዛሬስ ክብሬን በሰው መካከል ሊገልጥልኝ ነው ብሎ ሊቀበል ታጥቆ ተነሳ፡ ወደላይ ይዞበት ወጣ፡ ሀና እና ኢያቄምም ሊቀበሉ ተነሱ ወደላይ ይዞባቸው ወጣ ከዚህ ሁሉ ድርጊት በኋላ ዘካርያስ በቃለ አክብሮ ሀና! ምናልባት ለዚች ሕጻን የወረደ መንፈስ ቅዱስ ይሆናል ትተኻት ፈቅ በይ አላት እሷም ትታት ፈቀቅ አለች፤ ወርዶ የቆመ ብእሲ ያህል ከፍ አድርጎ አንድ ክንፋን አጎናጽፎ፤ አንድ ክንፋን ጋርዶ፤ መግቧት አርጓል፡ ካህናቱም የምግቧ ነገር ከተያዘልን ብልው ከቤተ መቅደስ አስገብተዋት ሄደዋል።

### ቤተ መቅደስ የቆየችበት ዘመን

ቤተ መቅደስ የቆየችበት ዘመን ከእናት ካባቷ ቤት ሶስት ዓመት፤ ከቤተ መቅደስ አስራሁለት ዓመት ጠቅላላ አስራ አምስት ዓመት ሲሆናት አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ይህች ብላቴና አቅመ አዳም አደረሰች ቤተ መቅደሳችንን ታሳድፍብናለች ትውጣልን፤ ብለው ለዘካርያስ ክስ አቀረቡ፡፡ “አ ወለተ እስራኤል ትፈቅድኑ ትንበሪ” አንቺ የእስራኤል ብላቴና ሆይ በዚሁ በቤተ መቅደስ መቆየት ትፈልጊያለሽን? አላት ወደ እግዚአብሐር አመልክትልኝ አንጂ እኔ ምን

አውቃለሁ አለችው፡ ወደ እግዚአብሐር ቢያመለክት ከቤተ ይሁዳ ሚስቱ የሞተችበትን ሰው በትር ሰብስበህ ከቤተ መቅደስ አስገብተህ ስትጸልይበት እደር ከዚያ ምልክት አሳይልሃለሁ፡ ያ ይጠብቃት አለው፡ ከቤተ ይሁዳ ሚስቱ የሞተችበትን ሰው በትር ቢሰበስብ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት በትር አገኘ፡ ለሁለት ሺህ አስራ አምስት የጎደለው መሆኑ ነው፡ ከቤተ መቅደስ አስገብቶ ሲጸልይበት ቢያድር ከዮሴፍ በትር "አ ዮሴፍ ወልደ ዳዊት እቅባ ለማርያም ፍኅርትከ" ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያምን ትጠብቃት ዘንድ አትፍራ የሚል ተጽፎ ተቀርጾ ተገኘ፡ ዕጣም ቢጣጣሉ ለእርሱ ወጣ፡ ርግብም ወርዳ በራሱ ላይ አርፋበታለች እንደሶስት ምስክር፤በዚያም በዚያም ብሎ ላንተ ወጣ ግብር ገብተን ሰጥተንሃል ብልው ሰጡት ከቤቱ ወስዶ አኖራት።

## ዜና ሞታ ለማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከእናት ካባቷ ቤት ሶስት ዓመት፤ከቤተ መቅደስ አስራ ሁለት ዓመት፤ ጌታን ጸንሳ ሳለች ዘጠኝ ውር ከአምስት ቀን፤ከጌታ ጋራ ሰላሣ ሶስት ዓመት ከሶስት ወር፤በቤተ ዮሐንስ አስራ አምስት ዓመት በአጠቃላይ በስልሳ አራት ዓመቷ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በዘመነ ሉቃስ ጥር ሃያ አንድ ቀን አርፋለች ፡ የጌታ ደቀ መዛሙርት ሐዋርያት ሊቀብሩ በአጎበር አድርገው ወደጌቴሴማኒ ይዘው ሲሄዱ መቼም አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ከዚህ አስቀሞ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስን ያልተነሳውን ተነሣ፤ ያላረገውን ዐረገ እያሉ ሲያውኩን ሲያስቸሩን ኖረዋል አሁን ደግሞ እሷን ተነሳች፤ ዐረገች፤ እያሉ ሊያውኩን አይደለምን? በእሳት አስከሬኗን እናቃጥላለን ብለው ተሰብስበው ሄዱ፡ከመካከላቸው ታውፋንያ የሚብል አይሁዳዊ ተራምዶ የእመቤታችን በድን ያለበትን አጎበሩን ጨበጠው፡ የታዘዘ መልአክ በስይፍ ሁለት እጁን ሰየፈው  እጁ ካጎበሩ ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ ነገር ግን የሁላችን እናት ድንግል ማርያም ነፍስ አዳኝ ናት እንጂ ነፍስ ገዳይ አይደለችምና እጆቹን በተአምራት ቀጥላለት እንደቀድሞው ሆነውለውታል፡በዚህ ጊዜ ዮሐንስን ጨምሮ በደመና ነጥቆ ከገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖራት ይሁን እንጂ ሐዋርያትም ዮሐንስን እመቤታችን እንደምን ሆነች አሉት በገነት ከዕፀ ህይወት ሥር ናት አላቸው፡ ለዮሐንስ ይህ ሁሉ ክብር ተገልጾለት እኛስ አናይምን? ብለው በነሐሴ መጀመሪያ ጾም ያዙ ሁለት ሱባዔ ጾመው በአስራ አራተኛው ቀን ሥጋዋን አምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረዋታል፡ በሶስተኛው ቀን ተነስታለች "ከመ ትንሣኤ ወልዳ" እንደ ልጇ ትንሣኤ ያሰኘውም ይህ ነው እንጂ ዕለቱን አይደለም፡

## ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር

ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ቶማስ ይህ ሁሉ ሲፈጸም አልነበረምና  ከሀገረ ስብከቱ በደመና ሲመጣ እርሷ ስታርግ አገኛት፤ "ወፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ" ብሎ ያመጣዋል ከደመናው ወርዶ ራሱን ማሳለፍ ወደደ፡ እንድህም አለ ቀድሞ የልጂሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ ዛሬ ደግሞ ያንቺን ትንሳሣኤ ሳላይ ቀረሁ ብሎ! እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አይዞህ አትዘን እነርሱ ትንሣኤየን፤ ዕርገቴን አላዩም አንተ ግን ትንሣኤየን ዕርገቴን አይተሃል እንዲያውም ተነሳች፤ዐረገች ብለህ ንገራቸው ብላ የያዘችውን ሰበን ሰጥታ ሰደደችው እሱም ከሐዋርያት ጋራ ትንሽ እንደተጨዋወተ የእመቤታችን ነገር እንደምን ሆነ?አላቸው እርሷንማ አግኝተን ቀበርናት አሉት" ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር" ተዉ ይህ ነገር አይመስለኝም አላቸው።ጴጥሮስ አንተ እንጂ ልማድህ ነው አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም ሌሎችንም ስታጠራጥር ትኖራለህ አለው፡ እሱም የያዘውን ያውቃልና ጸጥ ብሎ ይሰማቸዋል፡ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ "ወነሥአ ምክራዮ" ይለል መቆፈሪያውን ይዞ ተቆጥቶ ሄዶ መቃብሩን ቢከፍተው አጣት ደንግጦ ቆመ፡ አታምኑኝም ብየ ነው እንጂ እመቤታችንስ ተነሳች፤ ዐረገች አላቸው፡ ቶማስ ነው፤የያዘውንም ሰበን ሰጥቷቸው ለበረከት ተካፍለውታል በዚያ ሰብን ሙት ሲያስንሱበት፤ ድውይ ሲፈውሱበት ኖረዋል፡ ሰበን ማለት እንደመታጠቂያ ያለ ነው፡ ከዚህ በኋላ በዓመቱ ቶማስ  ትንሣኤዋን፤ዕርገቷን አይቶ አኛ ሳናይ ብለው እንደቀድሞው በነሐሴ መባቻ ጾም ጀመሩ ሁለት ሱባዔ ጨርሰው በአስራ ስድስተኛው ቀን ጌታ እመቤታችንን እንደመንበር አድርጎ ቀድሶ አቁርቧቸው እርሷንም "ወተቁርበት በዕደ ወልዳ" ይላል ያን ጊዜ በልጇ እጅ ቆርባለች "ዘጸውዓ ስመኪ ወዘገብረ ተዝካረኪ" ስምሽን የጠራ፤መታሰቢያሽን ያደረገ ብሎ ለእመቤታችን፤ "ዘጸውዓ ስመክሙ ወዘገብረ ተዝካረክሙ" ስማችሁን የጠራ፤ መታሰቢያችሁን ያደረገ ብሎ ለሐዋርያት ቃል ኪዳን ሰጥቷቸው ዐርጓል፡፡ዛሬም ቢሆን ማንኛውም አርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ሁሉ ቃል ኪዳኑን አጽንቶ፤  የእመቤታችንን አማላጅነቷን፤ በረከቷን በመማጸን በዓሉን በዝማሬ በዕልልታ  ያከብራል፤በመስቀሉ ይባረካል  በእምነቱ ይታሻል፡፤ይቆየን

የእመቤታችን አማላጅነቷ አይለየን፡አሜን

ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም

ሎንዶን ብሪታን

ከመ/ር ሔኖክ ቸሩ